# ለህብረቱ አገር አቀፍ ጉባኤ
# ከመኢሶን የቀረበ የአጀንዳ አስተዋፅኦ

አለም አቀፍ የነፃ ምርጫ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ እንኳን ቢሆን በግንቦቱ የምርጫ ሂደት በሙሉ ልብ ገብተን ለመሳተፍ ያደረግነው ውሳኔ ትክክለኛ ውሳኔ ነበር። ይህንን ስናደርግ በወያኔ/ኢህአዴግ የምርጫ ቦርድ ተማምነን ምርጫው በሃቅ ይካሄዳል ከሚል እምነት ተነስተን አልነበረም። የምርጫ ሂደት ስትራቴጂያችን ሁለት ገፅታዎች ነበሩት። አንደኛ ህዝባችንን በዚህ ባልተሟላ ሁኔታ እንኳን ቢሆን ከዳር እስከዳርና በገፍ ከተንቀሳቀሰ ወያኔ ኢህአዴግም የዚያኑ ያህል ከዳር እስከዳርና በገፍና አይን ባወጣ ሁኔታ አጭበርብሮ አሸንፍኩ ለማለት ይገደዳል። ያኔ ደግሞ ህዝባችን እንደዚህ ተንቀሳቅሶ ይህንን ድል ከተጎናፀፈ ጭብርብሩን ለመቋቋም በበቂ ተሰናድቷልና በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ዛሬ ያለንበት አለም ለተጭበረበሩ ምርጫዎች ያለው ትእግስት የተሟጠጠ ነውና በነዚህ ሁለት ክስተቶች ታግዘን ትግላችንን እንቀጥላለን ብለን ተንቀሳቅሰናል። በሁለተኛ ደግሞ ያለንበት ህገ መንግስታዊ ስርአት መድበለ ፓርቲ ምርጫ ስለማይፈቅድ በዚህ ምርጫ የምንሳተፈው መድበለ ፓርቲ ምርጫ እውን የሚሆንበት ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት ለማምጣት የሚደረገውን ትግል ለማገዝ እንደሆነ አስታውቀን በዚህ ምርጫ ካሸነፍን ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር ሆነን የመንግስት ስልጣን በመያዝ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ዘመን እንከፍታለን ብለን ተንቀሳቅሰናል።

የስትራቴጂያችን የመጀመሪያ ገፅታ ሙሉ በሙሉ በመሳካቱ ዛሬ ምናልባት ከየካቲት አብዮት ወዲህ በሃገራችን ያልታየ እኛም፤ ኢህአዴግም አለም አቀፉ ኮሙኒቲም ጨርሶ ያልጠበቀው አኩሪ ህዝባዊ ማእበል ተንቀሳቅሷል። አሁን በተጨባጭ ባለው ሁኔታ ኢህአዴግ በየምርጫ ወረዳው ይህ ነው የማይባል በገፍና አይን ባወጣ ሁኔታ በተካሄደ ጭብርብርና ሸፍጥ ብርታት ብቻ "አሸነፍኩ" ለማለት የተገደደበት የመጋለጥ ደረጃ ደርሷል። ህዝባችን በበኩሉ ደግሞ የትግሌንና የመስዋእትነቴን ፍሬ በጠራራ ፀሃይ ተነጠቅሁ እያለ ይህንን ድሉን መልሶ እጁ እንዲያስገባ ለሚያደርገው ትግል አመራር እየጠየቀ ነው። ኢህአዴግ በበኩሉ ይህንን ሽንፈት ለመቀበል ዝግጁ ስላይደለ በአንድ በኩል ህጋዊውን የውጤት ማጣራት ሂደት ከምርጫ ቦርዱ ጋር በመመሳጠር ለማደናቀፍ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህዝባዊው እንቅስቃሴ እንዲፈዝና እንዲከስም ባለ በሌለ ሃይሉ በአፈናና በተለያዩ የወከባ ስልቶች በመጠቀም እየተንቀሳቀሰ ነው። በአለም አቀፍ ደረጃ ታዛቢዎችን ጨምሮ ብዙ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ባእዳን ኢህአዴግ በከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠርም ተሸንፏል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል። በዚያው መጠን ደግሞ ባእዳን ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው ኢህአዴግ ሽንፈቱን ለመቀበል ዝግጁ ስላይደለ ተቃዋሚዎችም አገር ተረክበው ለማስተዳደር ዝግጁ ስላይደሉ አገሪቱ ወደ ትርምስ እንዳትገባ ከተፈለገ ሁለቱም ወገኖች ሁሉን አቀፍ የብሄራዊ አንድነት መንግስት ያቋቁሙ እያሉ ግፊት ማድረግ ላይ መሆናው የአደባባይ ምስጢር ነው። ይህ ደግሞ ወደ ህብረቱ የትግል ስትራቴጂ ሁለተኛ ገፅታ ያመጣናል።

የስትራቴጂያችን ሁለተኛ ገፅታ የምርጫ ማግስት መንግስት ጥያቄን የሚመለከት ነው። ህብረታችን በዚህ ጉዳይ ግልፅ የሆነ አቋም አለው። የግንቦቱ ምርጫ ዋና ተልእኮ ቀጣይነት ባለው ሰላማዊ፤ ህጋዊና ህዝባዊ ትግል ሃገራችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት የምትሸጋገርበትን ሁኔታ የማመቻቸት ተልእኮ ነው። ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ከዚህ ምርጫ በድል አድራጊነት ከወጡ በኛ እምነት የቀጣይ መንግስት ታሪካዊ ሚና በፕሮግራማችን ክፍል ሁለት *"ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ህብረተሰብ የሽግግር ሂደታችን"* በሚል በአስራ ሁለት ገፆች የዘረዘርናቸውን ተግባራት የማከናወን እንጂ በዚህ ህገ መንግስት ስር ለአምስት አመታት ሃገር የማስተዳደር ሚና ብቻ መሆን የለበትም። የህዝብ ድምፅ ውጤት ግልፅና በተለይ በህዝባችን አይን ተአማኒነት ባለው ሁኔታ እንዲጣራ የተጀመረው ህጋዊ ሂደት ፍትሃዊ እልባት እንዲያገኝ ከሚደረገው ትግል በተጓዳኝ ስለ ቀጣዩ መንግስት ተግባራት፤ የስልጣን ዘመንና ተልእኮ በማስመልከት ከማንም ይሁን ከማን ጋር የሚደረግ ማንኛውም ድርድር ከዚህ ግልፅና ዴሞክራሲያዊ አቋም ተነስቶ መካሄድ ያለበት ድርድር መሆን ይኖርበታል።

1. **የህዝባችንን ድል ሳናስነጥቅ ወደ ብሄራዊ አንድነት መንግስት ሃሳብ ማቅረብ**

ዛሬ በሃገር ውስጥም ሆነ በአለም ደረጃ "የህዝቡ ድምፅ ይከበር" በሚል ሚልዮኖች እየተንቀሳቀሱ እናያለን። ህብረታችን ይህንን እንቅስቃሴ መደገፍና እንዲያውም ለትግሉ አመራር መስጠት ይጠበቅበታል። ህብረታችን አሁን የ ተጀመረው ህጋዊ የማጣራት ሂደት ተአማኒነት ባለው ሁኔታ ተጣርቶ እንዲቋጠር በሚለው ምንም ፈቅ በማይል ዴሞክ ራሲያዊ፤ ፍትሃዊና ሰላማዊ አቋም መቀጠል ይኖርበታል። ያለው ትልቅ ችግር ህዝባችንም፤ እኛም፤ ኢህአዴግም፤ አለ ም አቀፍ ኮሙኒቲውም ይህ ህጋዊ የማጣራት ሂደት በትክክል እልባት ካገኘ ኢህአዴግ መሸነፉ ይረጋገጣል እንላለን። ኢህአዴግ ግን ይህንን ሽንፈት በፀጋ ለመቀበል ስላልተዘጋጀ "አዳኝ የከበበው አውሬ" (ፈረንጆቹ ኮርነርድ ካት ሳንድሮ ም የሚሉት አይነት) አፀፋ በመስጠት ሃገሪቱ ወደ ትርምስ ልትገባ ትችላለች የሚል ፍራቻ አለ። ኢህአዴግም በተለይ በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ አንፃር ይህንን ማስፈራሪያ እየተጠቀመበት ነው።

ይህ ቀውስ የተፈጠረው የኢህአዴግ መሪዎች ለአባሎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው ስልጣን ላይ የመቆየቱን ጉዳይ " የሞት ሽረት ጥያቄ" አድርገው በማቅረብና ስልጣን ላይ ለመቆየት በመፈፀም ላይ ያሉትን ግፍና አመፅ "ጅብ ከሚበላ ህ በልተህ ተቀደስ" በሚለው አባባል መሰረት የአልሞት ባይ ተጋዳይ አካሄድ አድርገው ስለሚያቀርቡት ነው። አለም አቀፉም ኮሙኒቲ ነገሩን የሚረዳው እንደዚህ ነው።

ሃገራችን በታሪኳ ምንም አይነት ሰላማዊ የሆነ የስልጣን ሽግግር ልምድ የላትም። ሁልጊዜ አሸናፊው ሁሉን የ ሚያፍስበት ተሸናፊ ሙልጭ የሚቀርበትና ለአሸናፊው ተንበርክኮ የሚገዛበት ሂደት ውስጥ ቆይተናል። ዛሬ የኢህአዴ ግ መሪዎች ይህ ፍራቻ ቢኖራቸው በተለይ ደግሞ ተራው አባልና ደጋፊ የዚህ ታሪካዊ ክስተት ሰለባ ሆኖ በምርጫ ከስ ልጣን መውረድን እንደ አለም መጨረሻ ቢያየውና ይህንን "አደጋ" ለመመከት የሞት ሽረት ትግል ላካሂድ ቢል ምን ም የሚያስገርም ነገር የለውም። ይህንን ጭንቀት ለማስተናገድ ስንል የህዝባችንን ድል አናስቀማም። ሆኖም ለህዝባች ንም፤ ለኢህአዴግ አባላትም፤ ለአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ተአማኒነት ያለው ከምንም አይነት አክራሪነት የራቀ ከኛም መሰረታዊ የሽግግር ስትራቴጂ የማይጋጭ ከቀውስ የመውጫ አስታራቂ ሃሳብ ይዞ መንቀሳቀስ ታሪክ የጣለብን ከባድ ሃ ላፊነት ሆኖ እናገኘዋለን።

የድምፅ ማጣራቱ ሂደት በሃቅ ከተካሄደ በድምፅ ብልጫ ማንም ያሸንፍ ማንም ከዚህ ከግንቦቱ ምርጫ ህብረ ተሰባችንና ዴሞክራሲ በድል አድራጊነት ወጥተዋል ብለን በአፍ ሙሉ መናገር እንችላለን። በፕሮግራማችን ስለ ብሄራ ዊ እርቅ ፖሊሲ፤ ስለ ዴሞክራታይዜሽን፤ ስለ ሽግግር መንግስት ያቀረብናቸው ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ አማራጮች ላ ይ እስከተመረኮዝንና ይህንን ህዝባዊ አላማ ሳንስት እስከተንቀሳቀስን ድረስ በምርጫው ማጣራት ማግስት አሸናፊና ተሸ ናፊ የማይኖርበት ኢህአዴግንም የሚጨምር የብሄራዊ አንድነት መንግስት ማቋቋም ምንም የሚያስጨንቀን ነገር መሆ ን የለበትም።

ከዚህም በመነሳት የህዝባችንን እምኔታ ሳናጣ በኢህአዴግም አባላት ሆነ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲው አካባቢ ያለ ውን ጭንቀት በማስተናገድ ወደ ፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ አጥቂነት ለመሸጋገር አራት ግልፅ ሃሳቦችን ማቅረብ እንችላ ለን።

አንደኛ የህዝባችን ድል እንዳይነጠቅ የማጣራቱ ሂደት ቀጥሎ ህጋዊና ፍትሃዊ እልባት እንዲያገኝ ለመታገል ያ ለንን ቁርጠኛነት ለሚመለከተው ሁሉ በተለይም ደግሞ ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ በግልፅ ማስታወቅ።

ሁለተኛ ይህ የማጣራት ሂደት እልባት ካገኘ የሰጠውን ውጤት ቢሰጥ ተቃዋሚዎችና ኢህአዴግ በአንድ ላይ ሆ ነው የብሄራዊ አንድነት የሽግግር መንግስት እንዲያቋቁሙ በይፋ ጥሪ ማድረግ።

ሶስተኛ በዚህ ሃላፊነት በሚሰማው የብሄራዊ እርቅና ዴሞክራሲያዊ አቋም ሙሉ በሙሉ እንደምናምንበት ለማ ረጋገጥ የማጣራቱን ውጤት ሳይጠብቁ ከወዲሁ ህብረት፤ ቅንጅትና ኢህአዴግ በአንድነት ሆነው የብሄራዊ አንድነት መንግስት ለማቋቋም መስማማታቸውን የሚገልፅ ሰነድ እንዲፈራረሙ መጠየቅ።

አራተኛ አለም አቀፉ ኮሙኒቲም በዚህ ሃሳብ ተስማምቶ ሁሉም ተፈራራሚ ወገኖች ለዚህ ስምምነት ተገዥ እን ዲሆኑ ባለው አቅም ሁሉ እንዲንቀሳቀስ ዲፕሎማሲያዊውን ትግል ማፋፋም።ሊጠየቅ ይችላል።

ይህ አካሄድ ለትግላችን በርካታ ጥቅሞች አሉት። አሁን እንደሚታየው ኢህአዴግና ምርጫ ቦርዱ እየተመሳጠ ሩ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁሉ ውድቅ በማድረግ የህዝቡን ድምፅ መርገጥ እስከዚህም የሞት ሽረት ጥያቄ ስለማይሆን

የማጣራቱ ሂደት በተሻለ ግልፅነትና ፍትሃዊነት እንዲቀጥል መንገድ ሊከፍት ይችላል። ሁለተኛ ደግሞ የህዝባችንን ድል ሳናስነጥቅ ኮምፕሮማይዝ ለማድረግ የምናሳየው ፈቃደኝነት በግልፅ ከታየና አክራሪ አቋም እንዳልያዝን ከታየ አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም በታዛቢነት በሚገኝበት የማጣራት ሂደት አይን ያወጡ ጭብርብሮች ሲካሄዱ ከታዘበ እነዚህን ለማጋለጥ ይበልጥ ቁርጠኛነት የሚያገኝበት ሁኔታ ይፈጠራል። ሶስተኛ በዚህ መልክ ማጣራቱ በተሻለ ፍትሃዊነት ከተካሄደ ተቃዋሚዎች የሚያገኙት መቀመጫ ከፍ ስለሚል ስለ ቀጣዩ መንግስት ምንነትና ተልእኮ የሚያቀርቡዋቸው ሃሳቦች ይበልጥ ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

## 2. የቀጣዩ መንግስት ተግባር፤ የስልጣን ዘመንና ተልእኮ ግልፅ አቋም ይዞ መደራደር

ከግንቦቱ ምርጫ የሚፈልቀው መንግስት ህብረታችን ለዚህ ምርጫ ከሰጠው ተልእኮ ውጭ ሊሆን አይችልም። ከፍ ብለን እንዳልነው የግንቦቱ ምርጫ ዋና ተልእኮ አሁን ካለንበት ፀረ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት ወደ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት፤ ሃገራችን ለዘመናት ተዘፍቃ ከቆየችበት የአመፅና የአሸናፊ/ተሸናፊ አዙሪት ተላቃ በብሄራዊ እርቅ ፖለቲካ ህብረተሰባችን በሙሉ ወደ ተረጋጋ ስርአት የሚሸጋገርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው። የሚያስፈልገን የሽግግር ዘመን መንግስት በፕሮግራማችን ክፍል ሁለት የተዘረዘሩትን የዴሞክራታይዜሽንና የብሄራዊ እርቅ ተግባራት እውን ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ መንግስት ነው።

ይህ መንግስት ይህንን ጥረት የሚያግዘው እሱ ራሱ ህብረተሰቡን ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ስርአት ለማሸጋገር በመስራት አይደለም። ይህ ሃላፊነት ከመንግስት ቁጥጥር ሙሉ በሙሉ ነፃ ለሆነ የዴሞክራታይዜሽን አካልና ለብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን መተው ይኖርበታል።

በዚህ ሂደት ኢህአዴግና ምናልባትም ቅንጅቱ ላይስማሙ ይችላሉ። ነገር ግን በዚህ ለኛ ቁልፍ በሆነ ጥያቄ ላይ ስምምነት ካልተደረሰና የሚቋቋመው መንግስት ባለው ህገ መንግስት ስር ሃገሪቱን ለአምስት አመታት ለማስተዳደር ብቻ የሚመሰረት ከሆነ ህብረታችን ኢህአዴግ ሰራዊቱን፤ ፖሊሱን፤ ደህንነቱን ወዘተ በሚቆጣጠርበት ሁኔታ እንዲህ አይነቱ የመንግስት ስልጣን የመጋራት ሂደት ውስጥ ከሚገባ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ አቋሙን እንደያዘ በተቃዋሚነት መቀጠሉ ይመረጣል። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ሁለቱ ሃይሎችም ሆኑ አለም አቀፍ ኮሙኒቲው ላይስማማበት የሚችል ግን ደግሞ በዴሞክራሲያዊነቱና በህዝባዊነቱ ምንም የማይወጣለት አቋም ይዞ ፍራያማ ድርድር ለማካሄድ ከፈለገ የህብረቱ አመራር በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ህዝባችንን ማሰለፍ ይኖርበታል። ይህ ሳይደረግ በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ አጋፋሪነት በየድርጅቶቹ መሪዎች ተወስኖ በዝግ ችሎት የሚካሄድ ድርድር ውስጥ መግባት ለእጅ ጥምዘዛ መመቻቸት፤ በዚህ መንግስት ውስጥ በተለጣፊነት ገብቶ የህዝባችንን ትግልና መስዋእትነት ለጥቂቶች ስልጣን መሸጥ ስለሚሆን ታሪካዊ የሆነ ስህተት እየፈፀምን ነው ማለት ነው።

እንግዲህ በኛ በኩል የታሰበው የተወዳዳሪዎች አገር አቀፍ ጉባኤ ሃላፊነት አሁን ካለንበት ውስብስብ ሁኔታ ወጥተን ይህንን ሁለት ገፅታ ያለው የትግል ስትራቴጂ በተግባር ለመተርጎም የሚያስችለን ስትራቴጂ የመቀየስና ይህንን በተግባር ለማዋል መወሰድ ስለሚኖርባቸው እርምጃዎች ለአባሎቻችን፤ ለደጋፊዎቻችንና ለኢትዮጵያ ህዝብ ግልፅ አማራጮች የማቅረብ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በመነሳት ጉዳኤው በሚከተሉት የአጀንዳ ነጥቦች ላይ እንዲወያይ ሃሳብ እናቀርባለን።

# አጀንዳ ነጥብ አንድ - የግንቦት 97 የምርጫ አጠቃላይ ሂደት መገምገም

1) ተቃዋሚዎች ማጆሪቲ አመጡ አላመጡ በአሁኑ ጊዜ በውል የታወቀ ነገር ባይኖርም አንድ እርግጠኛ የምንሆንበት ነጥብ በምርጫ ቦርድ የተሰጠው ውጤት በየአካባቢው ያለውን ሁኔታ በሃቅ የማያንፀባርቅና ሆን ተብሎ ያለው መንግስት አገኘ የሚባለውን ውጤት በማጋነን የቀረበ ውጤት ነው። እኛም ህዝባችንም ይህንን ሽፍጥ አንቀበለውም። ሆኖም የግንቦቱን ምርጫ ሂደት ስንገመግም በሶስት ነጥቦች ዙሪያ ውይይት ማካሄድ ያስፈልጋል

ሀ) የተጭበረበሩ ምርጫዎችን አሻፈረን ብለው በተለያዩ ሃገሮች ህዝቦች ታግለው ድል ያደረጉት ስለተደረገው
ሸፍጥ ግልፅና ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎች በማቅረብ ህዝቦቻቸውና አለም አቀፉ ኮሙኒቲውን ከጎናቸው በማሰለፋቸው
ነው። በመሆኑም ስለአጠቃላዩ ሂደትና ስለተፈፀሙት ህገ ወጥ ድርጊቶች ቀደም ሲል በተላለፉት ፎርሞች በመመራት
ሁሉም ተሳታፊዎች በየአካባቢው የሆነውን ሁኔታ በሃቅ መዝግበው መምጣትና ይህንን በአንድ በኩል እንዳለ በሪፖር
ት መልክ እንዲወጣ ማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ኮሚቴ ሰይሞ ከነዚህ ሪፖርቶች በመመርኮዝ በኤክዘኩቲቭ ሰ
መሪ መልክ አንድ አጭር ጭማቂ ሰነድ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል።ይህ ሰነድ በጉባኤው ማግስት ለኢትዮጵያ ህ
ዝብም ለአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ይፋ ይሆናል።

ለ) ምርጫው መጭበርበሩ የአለ ሃቅ ቢሆንም ይህ ማጭበርበር የምርጫውን አጠቃላይ ውጤት እስከመበከልና
እስከ መቀየር የሚሄድ አይደለም ከተባለና ኢህአዴግ "አሸነፍኩ" ያለው በሃቅ ሆኖ ከተገኘ ጉባኤው ይህ የሆነው እኛ
እራሳችን አማራጫችንን ለህ-ዝብ ስናቀርብ በተለያዩ የው-ስጥ ድግመቶችና የስትራቴጂ ስህተቶች በህዝባችን ፊት በ
ቂ ተአማኒነት ባለማግኘታችን እንደሆነ በይፋ አምነን መቀበል ይኖርብናል። ነገር ግን ደግሞ በያለበት የተከሰቱት ፀረ
ነፃ ምርጫና ህገ ወጥ ድርጊቶች ተደማምረው በሚደረገው ስሌት ኢህአዴግ በአሸናፊነት ወጣሁ ያለው በማጭበርበር
ብርታት መሆኑ ከተረጋገጠ ይህንን በማስረጃ በተደገፈ ሪፖርት ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለአለም አቀፍ ኮሙኒቲው አ
ስታውቆ ጉባኤው ይህንን ውጤት እንደማይቀበል ይፋ ያደርጋል። በሰላማዊ፤ ህጋዊና ህዝባዊ ትግል ስልት የተቀማውን
የህዝብ ድል ለማስመለስ ትግሉ ስለሚቀጥልበት ሁኔታ ስትራቴጂና ታክቲክ ይቀይሳል።

ሐ) በአሁኑ ወቅት ተቃዋሚዎች ሁለት መቶ ሃምሳ በሚጠጉ የም-ርጫ ወረዳዎች ኢህአዴግ በሸፍጥ አሸንፏል
በማለት ክስ መስርተው እነዚህን አቤቱታዎች ለመስማትና ለማጣራት አጣሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ እንደሰራ ስምምነት ተደ
ርሶ የማጣራት ሂደት ቢጀመርም በምርጫው ወቅት እንደታየው ሁሉ አሁንም ኢህአዴግና የምርጫ ቦርዱ እየተመሳጠ
ሩ ጭብርብርን ለማጣራት የተጀመረው ሂደት በጭብርብር የመጠናቀቅ አደገኛ አዝማሚያ እያሳየ ነው። እዚህም ላይ
በምርጫው ሂደት አንፃር ከያዝነው አቋም የተለየ አካሄድ አይኖረንም። የተጭበረበሩ ምርጫዎች ይጣሩ ብለን የመሰ
ረትናቸውን ክሶች የማጣራቱ ሂደት ራሱ አይን ባወጣና ከስምምነት ውጭ በሆኑ አሰራሮች በኢህአዴግና በምርጫ ቦር
ዱ ከተጭበረበረ ልክ ከፍ ተብሎ በነጥብ 'ሀ' እንደተጠቀሰው በዚህም አጣሪ ኮሚሽን አሰራር የተፈፀሙትንና በመፈፀ
ም ላይ ያሉትን ህገ ወጥና ከስምምነት ውጭ የሆኑ አሰራሮችን በማስረጃ በማጋለጥ የህዝቡን ድል ለማስከበር ስለሚደ
ረገው ቀጣይ ትግል ተወያይቶ አንድ ስትራቴጂ መንደፍ ይጠበቅበታል።

## አጀንዳ ነጥብ ሁለት - ሃገሪቱ ካለችበት የፖለቲካ አጣብቂኝ እንድትወጣ ስለምናቀርበው አማራጭ መወያየት

ከፍ ብለን በሰፊው እንዳቀረብነው የህዝባችንን ድል ሳለማስነጠቅ በምንም አይነት በማይበገር ቁርጠኛነት ተንቀ
ሳቅሰን ለህዝባችንም የሰከነ አመራር ለመስጠት ስንሰራ እዛው በዛው ደግሞ ህብረታችን በዴሞክራሲያዊ ሂደት ወደ ዴ
ሞክራሲያዊ ህገ መንግስትና ወደ ተረጋጋ ህብረተሰብ ለመሸጋገር ካቀረበው አማራጭ ፈቅ ሳይል ከወዲሁ **በሃቅ በተጠ
ራ የም-ርጫ ውጤት ላይ ተመርኩዞ** የብሄራዊ አንድነት መን-ግስ-ት የሚል የብሄራዊ እርቅ ፖሊሲ ማራመድ ይኖርበ
ታል። ጉባኤው ይህንን ከቀውስ መውጫ የሚሆን ሃሳብ ተቀብሎ ለኢትዮጵያ ህዝብም፤ ለኢህአዴግ ደጋፊዎችና አባላ
ትም፤ ለአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም በግል-ፅና በይፋ ማቅረብ ይኖርበታል። ይህንን ሲያደርግ ደግሞ ይህንን ሃሳብ በሚከ
ተሉት ዝርዝር ነጥቦች አጠናክሮ መሆን ይኖርበታል

ሀ) ይህ የብሄራዊ አን-ድነት መንግስት ዋና ተግባሩ ህብረተሰባችንን ወደ ዴሞክራሲያዊና በብሄራዊ እርቅ ላይ
ወደ ተገነባ የተረጋጋ ህ-ብረተሰብ ለማሸጋገርና በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት መድበለ ፓርቲ ምርጫ በሁለት
ሶስት አመታት ውስጥ የሚካሄድበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚሰራ መንግስት አድርገን እንደምናየው ማረጋገጥ

ለ) የዚህን የሽግግር ዘመን ተግባር በተመለከተ ህብረታችን በነደፈው አማራጭ ፕሮግራሙ ክፍል ሁለት የተዘረ
ዘሩ ተግባራትና እነዚህን በተግባር ለመተርጎም ከማንም ይሁን ከማንም መን-ግስት ነፃ የሆኑ አካላት ስለማስፈለጋቸው በ
ትክክል አስቀምጧል። ይህ ጉባኤ ከህ-ብረታችን ፕሮግራም በተለይ በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን አማራጮች በጥምና ተ

ወያይቶባቸው፤ እነዚህን ነጥቦች ይበልጥ ተጨባጭ፤ ይበልጥ ግልፅና ይበል-ጥ ተአማኒነት ባለው መልክ አዳብሮ ለኢትዮጵያ ህዝብም፤ ለሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶችና ዴሞክራቶችም፤ ለኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲም ማቅረብ

ሐ) የህብረታች-ን አካሄድ በዚህ መልክ በግልፅ ከተቀመጠ በሁዋላ ጉባኤው የህብረቱ አመራር ይህንን አቋም ይዞ ጉዳዩ ከሚመለከታው ሃይሎች ጋር በሙሉ እንዲደራደርና እነዚህን ዴሞክራሲያዊ፤ ሰላማዊና የብሄራዊ አጀንዳዎች ለማራመድ በፖለቲካውና በዲፕሎማሲው መስክ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ እንዲንቀሳቀስ ስለሚወክልበትና አጠቃላዩን ሂደት ስለሚከታተልበት ሜካኒዝሞች ተወያይቶ ውሳኔና መመሪያ መስጠት።

## አጀንዳ ነጥብ ሶስት - በጭብርብሩ ከተገፋና የብሄራዊ እርቅ ሃሳቦች ተቀባይነት ካላገኙ

ህብረታችን ለሃገር ለወገን አለኝ ከሚለው የሃላፊነት ስሜት በመነሳት የሚያቀርበውን ሃሳብ የኢህአዴግ መሪዎች አንቀበልም ሊሉ ይችላሉ። አልፈው ተርፈውም በተጭበረበረ የምርጫ ውጤትና በተጭበረበረ የምርጫ ውጤት ማጣራት ሂደት ተመርኩዘው አሸነፍን ብለው ሊያውጁ ይችላሉ። ይህ ከሆነ የህዝባችንን ድምፅ ለማስከበር ሰላማዊና ህጋዊ ትግላችንን በሰከነና በአገር አቀፍ ደረጃ በተቀናጀ መልክ እንዴት እንደምንቀጥል ጉባኤው በግልፅ ተወያይቶ አንድ አቋም ላይ መድረስና ይህንንም ለኢትዮጵያ ህዝብና ለሚመለከተው ሁሉ ከወዲሁ በይፋ ማስታወቅ ይኖርበታል። ህዝባችን፤ በውጭም በውስጥም ያሉ የሃገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች፤ የሲቪክ ማህበረሰቡ አባላት በሙሉ በአንድነት ሆነው "የህዝቡ ድምፅ ይከበር" በሚል በአንድና በአንድ መፈክር ዙሪያ ብቻ ስለሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ በጥሞና መወያየት ያስፈልጋል። ህዝባችን በቁጣና በግብታዊነት ተራ በተራ እየተነሳ ተራ በተራ ለኢህአዴግ አፈና ሰለባ እንዳይሆን፤ በኢህአዴግ በራሱ ስውር ደባ ሊከሰቱና ትግሉን ስርአት አልበኛና ህገ ወጥ ሊያስመስሉ ለሚችሉ ለከፋዎች እንዳይመቻች ጉባኤው በሚከተሉት ነጥቦቹ ዙሪያ ቢወያይ መልካም ይመስለናል

ሀ) የኢህአዴግ የምርጫ ቦርድ ስምምነቶችን ሁሉ እየጣሰ በሸፍጡ ገፍቶና ህጋዊው ሂደት ተሟጦ የኢህአዴግን የሸፍጥ ድል ካወጀ ህዝባችን በቁጣና በግብታዊነት እየተነሳ ለኢህአዴግ ደባ እንዳይመች በግልፅ ጥሪ አድርጎ ከዚህ በተጓዳኝ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በጠቅላላው ተቃዋሚ ድርጅቶችን፤ የሲቪክ ማህበረሰቡ ተወካዮችን፤ አለም አቀፍ ታዛቢዎችን ከተቻለ በውጭ አገሮች በኮሚቲ እየተደራጁ የህዝቡ ድምፅ እንዲከበር የሚታገሉ ዜጎች ተወካዮችን እንዲሁም የሃገር ሽማግሎችን ያካተተ አንድ አስቸኳይ አገር አቀፍ ጉባኤ ስለመጥራት መወያየት፤ መወሰንና ይ-ህንን በይፋ አስታውቆ የጉባኤ አዘጋጅ አካል መሰየም

ለ) የኢህአዴግ ስትራቴጂ የህዝባችን ትግል በግብታዊ ግንፋሎት መልክ እንዲካሄድ በመሆኑ ሰላማዊና ህጋዊ ተቃውሞ በሰከነ መልክ ለማካሄድ የሚጠራውን ይህንን አስቸኳይ አገር አቀፍ ጉባኤ ሊከለክል ይችላል። ይህ የተወዳዳሪዎች ጉባኤ በዚህም ጉዳይ ተወያይቶ በማንኛውም ህገ ወጥና ፀረ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ይህንን አስቸኳይ አገር አቀፍ ጉባኤ ከተከለከለ የህብረቱ አመራር ከሌሎች ተቃዋሚ ሃይሎች ጋርና ከተለያዩ የሲቪክ ማህበረሰቡ ተወካዮች ጋር መክሮ አገር አቀፍ የስራ ማቆም እንቅስቃሴም ሆነ ሌሎች ህጋዊና ሰላማዊ የትግል ስልቶች እንዲቀይስ ውክልና መስጠት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልት ተንቀሳቅሶ ድሉን እንዲያስመልስ ጥሪ ማድረግ

ሐ) በመላው አለም ተሰራጭተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጥረታቸውን ከአሁኑ ይበልጥ አቀናጅተው በሃገር ውስጥ የሚደረገውን ተጋድሎ ከመንግስታት፤ ከመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ ከሰብአው መብት ተሟጋቾች ስብስቦችና ከሌሎች አግባብ ካላቸው ሃይሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለህዝባችን ትግል አለም አቀፋዊ ድጋፍ ለመሰብሰብ መታገልና ይህንን ትግል በፋይናንስና በማቴርያል ለማገዝ እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ ማድረግ።

## አጀንዳ ነጥብ አራት - በጉባኤው ማብቂያ የድጋፍ ስልፎች ስለመጥራት

የዚህ አገር አቀፍ የተወዳዳሪዎች ጉባኤ አንዱ አላማ በሃገር ደረጃ የሚደጋገፍ የህዝባዊ ትግል ማእበል መቀስ ቀስ ነው። ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ዜጎች የሚተዋወቁበት፤ እያንዳንዱ ታጋይና እያንዳንዷ ታጋይ ብቸኛ ሳይሆኑ የአንድ ሰፊ አገር አቀፍ ታሪካዊ ተጋድሎ አካል መሆናቸውን ግንዛቤ የሚወስዱበት አጋጣሚ ነው። በዚህ ጉባኤ ላይ የ ሚወሰዱ ውሳኔዎችና የሚቀየሱ የትግል አቅጣጫዎች ፍሬያማ የሚሆኑት ህዝባችን ይዘታቸውን ጠን-ቅቆ ተረድቶ ብሄ ር፤ ቋንቋ፤ ሃይማኖትና ክልል ሳይል በጋራ ሲዋደቅላቸው ብቻ ነው። በመሆኑም ስለትግሉ አላማ ለህዝባችን ግንዛቤ ለ ማስጨበጥ በሚቻልበት ቦታ ሁሉ ሰላማዊ ሰልፎች ለመጥራት ጉባኤው መወሰን ይኖርበታል። እነዚህ ሰልፎች በሶስት ሸንሸኖ ማየት ይቻላል።

አንደኛ ተወዳዳሪዎች በየመጡበት ተመልሰው ከተቻለ በመላ በሃገሪቱ በአንድ በቅድሚያ በተቆረጠ ቀን ሰላማ ዊ ሰልፎች ቢጠሩ ለትግሉ ቅንብር፤ ትግግዝና አገር አቀፋዊነት ትልቅ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው በዚሁ ጉዳይ አንድ ውሳ ኔ መድረስ

ሁለተኛ የጉባኤው ተሳታፊዎች አዲስ አበባ መገኘታቸውን አጋጣሚ በመጠቀም ወደየመጡበት ከመመለሳቸው በፊት የህብረቱ አመራርና የሌሎች ዴሞክራሲያዊ ድ-ርጅቶች መሪዎች እንዲሁም ከየክልሉ አንድ ተወካይ መልእክት የሚያስተላልፉበት አንድ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ አዲስ አበባ ለመጥራት መወሰንና መዘጋጀት

ሶስተኛ በአለም አቀፍ ደረጃም የጉባኤው ውሳኔዎች ለኢትዮጵያን ባፋጣኝና በሰፊው እንዲደርሱ አድርጎ በያለ በት የተቀነባበሩ ሰልፎች እንዲደረጉ ጥሪ ማድረግ።

**የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)**
ሃምሌ 1997 ዓ.ም.